የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

Ministry of Women and Social Affairs

# የህፃናት ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት ማቋቋሚያ መስፈርት እና አሰራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1084/2017 ማብራሪያ

## 1. መግቢያ

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት መሰረት በማድረግ የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አካልጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መሰረታው መብትና ፍላጎቶች ለማስከበርና ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ በተለይም የሴቶችና ህጻናትን መብት፣ ደህንነት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሻሻል ከተቀረጹ ፕሮግራሞች መካከል የህጻናት የቀን ማቆያና መንከባከቢያ አገልግሎት አንዱ ነው፡፡ ይህ አገልግሎት በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እድሜያቸው ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ያልደረሱ ህጻናትን ለዕደገታቸው አወንታዊ ሚና በሚጫወት አያያዝ የመንከባከብ ሂደት ነው፡፡

የህጻናት የቀን ማቆያና መንከባከቢያ አገልግሎትን ጥራትና ደረጃውን ጠብቆ ማስፋፋትና ማጠናከር ከህጻናት መብትና ደህንነት፣ ሴቶችን ከማበረታታትና ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸውን ከማሳደግ፣ የስርዓተ ጾታ እኩልነትን ከማስፈን፣ የቤተሰብ ገቢን ከማሳደግ፣ የስራ እድል ከመፍጠር፣ የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥ እንዲሁም ንቁ እና አምራች ሃገር ተረካ ዜጋን ከማፍራት አንጻር በርካታ ጥቅሞች ይኖሩታል፡፡

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የህጻናት የቀን ማቆያና መንከባከቢያ ሊኖሩት የሚችሉትን በርካታ ጥቅሞች በመረዳት በተለይም በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚቋቋሙ የህጻና ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላትን ከማስፋፋትና ከማጠናከር ባለፈ አገልግሎቱ  ከመንግስት የስራ ቦታዎች ውጪ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችና ሁሉም ህጻናትን በሁሉም የሃገራችን ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ በዚህም ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የግንዛቤና የተሞክሮ ልውውጥ መድረኮችን በማመቻቸት፣ ሙያዊ ድጋፎችን በማድረግ፣ የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በመስራት፣ ባለፉት ስድስት አመታት በርካታ ቁጥር ያላቸው የህጻናት ማቆያዎች በመንግስትና በግል ዘርፍ ባሉ የስራ ቦታዎች፣ በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ በግል የንግድ ዘርፍ፣ እና በሌሎች ዓይነቶች እየተቋቋሙ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ የአገልግሎቱ ፈላጊዎች እና አገልግሎት አቅራቢዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሆኑን በተለያዩ ጊዚያት የሚሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን የህጻና ማቆያ አገልግሎት ማስፋፋትና ሴቶችና ህጻናትን ተጠቃሚ ማድረግ የሚኖረው ሃገራዊ ጠቀሜታ እንዳለ ሆኖ በዋናነት የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ህጻናት እንደመሆናቸው ከስጋትና ጥቃት ተጋላጭነት ነጻ የሆነ፣ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሁም መብት እና ደህንነታቸውን ያስጠበቀ አገልግሎት መስጠት ይቻል ዘንድ በልዩ ትኩረትና በስርዓት ሊመራ ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የህጻናት ማቆያ አገልግሎት ጥራትና ደረጃውን ጠብቆ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሚሰሩ ስራዎች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው የስርዓት ዝርጋታ ስራ ሲሆን የተጠናከረ የህጻናት ማቆያ ስርዓትን ለመዘርጋ ይቻል ዘንድ ይህ የህፃናት ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት ማቋቋሚያ መስፈርት እና አሰራር ለመወሰን የሚረዳ መመሪያ

ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. የመመሪያ ዝግጅት ሂደት

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶችና የህጻናትን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ በአዋጅ ሃላፊነት እንዳለበት መንግስታዊ አካል የፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች የህፃናት ማቆያ የአሰራር መመሪያ በ2010 ዓ.ም አዘጋጅቶ ስራ ላይ እንዲውልና በመንግስት መስሪያቤቶች ዘንድ ተፈጻሚ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡

በ2010 ዓ.ም የወጣው መመሪያ በመንግስት አስፈጻሚ ተቋማት ውስጥ የሚቋቋሙ ማቆያዎችን ብቻ እንጂ በሌሎች አካላት የሚቋቋሙ የህጻናት ማቆያዎችን የማይመለከት በመሆኑ አገልግሎቱን ወጥ በሆነ መልኩ ለመምራት ይቻል ዘንድ በሁሉም አካላት የሚቋቋሙ የህጻናት ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት የሚመሩበት የአገልግሎት መስጫ መስፈርት በማዘጋጀት ወደስራ ማስገባት ይቻል ዘንድ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍተኛ የስራ ሃላፊዎች ለማቅረብ የተቻለ ሲሆን የአገልግሎት መስጫ መስፈርቱ የህጻናት ማቆያዎች ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲያቀርቡ በማድረግ  የህጻናትን መብት እና ደህንነት የሚያስጠብቅ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ነገር ግን የተዘጋጀውን መስፈርት በሁሉም አይነት የህጻናት ማቆያዎች ላይ በአስገዳጅነት ተግባራዊ ለማድረግ የህግ መሰረት የሚያስፈልግ በመሆኑ ቀደም ብሎ  በመንግስት የስራ ቦታዎች የሚቋቋሙ የህጻናት ማቆያዎችን ብቻ በሚመለከት የተዘጋጀውን መመሪያ በማሻሻል/በመሻር፤ ሁሉም አይነት ማቆያዎች የሚመሩበት የህግ ማዕቀፍ (መመሪያ ወይም ደንብ) እንዲዘጋጅ እና የአገልግሎት መስጫ መስፈርቱ በአዲስ መልክ የሚዘጋጀው መመሪያ አካል ወይም የመመሪያው ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሆኖ እንዲቀርብ አቅጣጫ አስቀምጠዋል፡፡

በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የተቋሙን የህግ ክፍል ጨምሮ ጉዳዩ በዋናነት ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች የተውጣጡ ባለሙያዎችና ሃላፊዎች የተወከሉበት የመመሪያ ዝግጅት ቡድን በማዋቀር ቀደም ብለው የነበሩ ሰነዶችን እና የዳሰሳ ጥናት ውጤቶችን መነሻ በማድረግ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ ረቂቅ መመሪያውን ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት በማቅረብና ግብዓቶችን በማሰባሰብ፣ የተሰጡ ግብዓትና አስተያየቶችን አግባብነት በመፈተሽ በመመሪያው ውስጥ በማካተት፣ መሪያውን ለማዳበር የሚረዱ የግብዓት ማሰባሰቢያ መጠይቆችን አዘጋጅቶ ዳሰሳ ጥናት በማድረግ እንዲሁም የተዘጋጀውን ረቂቅ መመሪያ የሴ/ማ/ጉ ሚኒስቴር የስራ ክፍል ሃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ የተጠናቀቀውን መመሪያ ለመጀመሪያ ዙር አስተያየት ወደ ፍትህ ሚኒስቴር ለመላክ ተችሏል፡፡ በፍትህ ሚኒስቴር የተሰጡ የማስተካከያ ግብዓቶች መሰረት መመሪያውን በማዳበር ይህ የመጨረሻ መመሪያ ተዘጋጅቶ በፍትህ ሚኒስቴር እንዲመዘግብልን ቀርቧል፡፡

### 3. የተካሄዱ የግብዓት ማሰባሰቢያ፣ የውይይት መድረኮችና መመሪያውን የማደበር ሂደቶች

በዚህ መመሪያ ዝግጅት ሂደት ጉዳዩ በዋናነት የሚመለከታቸው እና ግብዓት ሊሰጡ ይችላሉ ተብለው ለታሰቡ አካላት መድረኮችን በማመቻቸት መመሪያውን በማቅረብ ግብዓቶችን ለማሰባሰ፤ና ውይይቶችን ለማድረግና መመሪያውን ለማዳበር ተችሏል፡፡

| ተ.ቁ | በመመሪያ ዝግጅት፣ በግብዓት ማሰባሰብ እና በውይይት መድረክ ተሳታፊ የሆኑ አካላት | ቀን | ቦታ |
|---|---|---|---|
| 1 | ከሴ/ማ/ጉ/ሚ/ር የተለያዩ የስራ ክፍሎች በተውጣጡ ባለሙያዎች እና ሃላፊዎች ውይይት በማድረግ የመጀመሪያ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል፤ | ጥቅምት 2016 ዓ.ም | አዲስ አበባ |
| 2 | የተዘጋጀውን ረቂቅ መመሪያ ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ከመቅረቡ በፊት የሚኒስቴር መስሪያቤቱ የስራ ክፍል ሃላፊዎች/ስራ አስፈጻሚዎች እንዲያዩት እና ግብዓት እንዲሰጡበት ተደርጓል፤ | ህዳር 2016 ዓ.ም | አዲስ አበባ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ከILO ጋር በመተባበር በግሉ ዘርፍ ያሉ የተለየዩ የአምራች ኢንዱስትሪ ማህበራት ተወካዮች ረቂቅ መመሪያው ቀርቦላቸው ግብዓት እንዲሰጡበት ተደርጓል፤ | የካቲት 2016 ዓ.ም | አዳማ |
| 4 | የፌዴራል መንግስት መስሪያቤቶች የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካ ትግበራ ፎረም ዓመታዊ ግንኙነት መድረክ ላይ መመሪያውን በማቅረብ ግብዓቶችን ለማሰባሰብ ተችሏል፤ | የካቲት 2016 ዓ.ም | አዳማ |
| 5 | በገጠር ልማታዊ ሴፍቲኔት የህጻናት ማቆያ ፓይለት ፕሮጀክት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከተመረጡ አምስት ክልሎች (ኦሮሚያ፣ ትግራይ፣ ሲዳማ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ደቡብ ኢትዮጵያ) የሴፍቲኔት ፕሮግራም የህጻናት ማቆያ አስተግባሪ ተቋማት (ግብርና፣ ሴቶችና ህጻናት፣ ጤና፣ ማህበራዊ፣ ትምህርት) ተወካዮች በተገኙበት መመሪያውን በማቅረብ ግብዓት ለማሰባሰብ ተችሏል፤ | መጋቢት 2016 ዓ.ም | ደብረ ዘይት |
| 6 | የተመረጡ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ ተቋማት ተወካዮች እና የሴ/ማ/ጉ/ሚ/ር የስራ ክፍሎች ተወካዮች መመሪያው ቀርቦላቸው ውይይት እንዲያደርጉበትና ግብዓት እንዲሰጡበት ተደርጓል፤ | መጋቢት 2016 ዓ.ም | አዳማ |
| 7 | ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የግሉ ዘርፍ አምራች ኢንዱስትሪ ማህበራት ተወካዮች በመመሪያው ላይ ውይይት እንዲያደርጉበትና ግብዓት እንዲሰጡበት ተደርጓል፤ | ሚያዝያ 2016 ዓ.ም | ድሬዳዋ |
| 8 | ከሁሉም ክልሎች የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ክፍል ሃላፊዎች/ተወካዮች መመሪያው ቀርቦላቸው ግብዓት እንዲሰጡበት ተደርጓል፤ | ሚያዝያ 2016 ዓ.ም | አዲስ አበባ |
| 9 | የመመሪያ ዝግጅት ቴክኒካል ቡድን አባላት በተለያዩ የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች የተነሱና መመሪያው ለማዳበር የተነሱ ነጥቦችን አንድ በአንድ በመፈተሸ፣ ተገቢውን ክብደት በመስጠትና በመመሪያው ውስጥ መካተት ያለባቸውን ቁልፍ ጉዳዮች በማካተት የመመሪያውን የመጨረሻ ይዘት የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ | ሚያዝያ እና ግንቦት 2016 ዓ.ም | አዲስ አበባ |
| 10 | የተዘጋጀውን መመሪያ ለፍትህ ሚኒስቴር መላክና አስተያየት መቀበል፡፡ | ሰኔ 2016 ዓ.ም | |
| 11 | ማብራሪያ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ዙሪያ በፍትህ ሚኒስቴር የህግ ማርቀቅ ስራ ክፍል ሃላፊዎች ጋር መነጋገርና ቀጣይ አቅጣጫዎችን መቀበል፡፡ | መጋቢት 2017 ዓ.ም | |
| 12 | በተሰጠው ግብዓት መሰርት መመሪያውን ማስተካከል፣ ማጠናቀቅና የእንግሊዝኛ ትርጉም ማዘጋጀት፡፡ | ሚያዝያ 2017 ዓ.ም | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 15 | ለምዝገባ ወደ ፍትህ ሚኒስቴር መላክ፤ | ግንቦት 2017 ዓ.ም | |

**4. መመሪያውን የማውጣት ስልጣን ምንጭ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 36 መሰረት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውስጥ፤ የሴቶች፣ ወጣቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያንና የሌሎች ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ሕጎችን ማመንጨት፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ማዘጋጀት በሚል የተሰጠውን ስልጣን እና በዚሁ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 19(4) መሰረት በማድረግ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

**5. የመመሪያው አስፈላጊነትን በተመለከተ**

በሃገራችን እየተስተዋለ ባለው የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦች ምክንያት የህጻናት የቀን ማቆያና መንከባከቢያ አገልግሎት ፈላጊዎችና የአገልግሎቱ አቅራቢዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ እንዲመጣ አድርጓል፡፡ ይህ በመልካም ጎኑ የሚታይ ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያቤታችንም አገልግሎቱን በተለያዩ ዓይነቶች ለማስፋፋትና ለማጠናከር በ10 ዓመት የልማ ዕቅዱ ውስጥ አካቶ እየሰራበት ይገኛል፡፡ ነገር ግን ተቀዳሚ ተጠቃሚዎች ህጻናት በመሆናቸው የህጻናት ማቆያና መንከባከቢያዎችን ከማስፋፋት ባለፈ አገልግሎቱ የሚመራበት ህጋዊ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በዚህም መሰረት በ2010 ዓ.ም በመንግስት መስሪያ ቤቶች ለሚቋቋሙ የህጻናት ማቆያዎች የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ቢሆንም ከመንግስት የስራ ቦታዎች ውጪ ያሉ የህጻና ማቆያ አገልግሎት ፍላጎት ተደራሽ ለማድረግ በተለያዩ አካላት የሚቋቋሙ የህጻናት ማቆያዎችን የማይመለከት በመሆኑ በሁሉም ዓይነት የህጻና ማቆያዎች ተግባራዊ ለማድረግ እንዳይቻል አድርጎታል፡፡ በመሆኑም ሃገራችን ከተቀበለቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ አንዱ በሆነው በተባበሩት መንግስታት የህጻናት መብቶች ስምምነት አንዱ መርህ በህጻናት መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት አለመፍጠር የሚል በመሆኑና የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የህጻናን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ በተቀዳሚነት የሚሰራ በመሆኑ በሁሉም የሃገራችን ክፍሎች የሚቋቋሙ የህጻናት ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት ለሁሉም ህጻና ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ማቅረብ ያስችላቸው ዘንድ ይህንን መመሪያ ማዘጋጀትና ስራ ላይ ማዋል አስፈልጓል፡፡

**6. የመመሪያው ዋና ዋና ይዘቶች**

መመሪያዉ አምስት /5/ ክፍሎች፣ ሃያ ሁለት /22/ አንቀጾች እና አንድ መቶ አምስት /105/ ንዑስ አንቀጾች ያሉት ሲሆን በሚከተለው መልኩ የተደራጀ ነው ፡፡

**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

1. አጭር ርዕስ
2. ትርጓሜ

3. የተፈጻሚነት ወሰን

4. የመመሪያው ዓላማ

**ክፍል ሁለት**

**የህጻናት ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት እና ሊያሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች**

5. የህጻናት ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት ዓይነቶች

6. ለህጻናት ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት **የብቃት ማረጋገጫ ስለመስጠት**

7. **የማዕከሉ አካባቢያዊ ሁኔታ**

8. **የማዕከሉ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች**

9. **የማዕከሉ መገልገያ ቁሳቁሶች**

10. **ለማዕከሉ የሚያፈልገው የሰው ኃይል**

11. **የህጻናት ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት ሰራተኞች ሊያሟሉ ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤**

**ክፍል ሦስት**

**የህጻናት ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከል አገልግሎት ዓይነትና አሰጣጥ ስርዓት**

12. የአገልግሎት ዓይነቶች

13. የአገልግሎት አሰጣጥ

14. **ስለህጻናት መቀበያ ዕድሜ**

15. **ለህጻናት ምዝገባ ስለሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች**

16. **የማቆያ ማዕከሉ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም**

**ክፍል አራት**

**የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ሃላፊነት**

17. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

18. የማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት ተግባርና ኃላፊነት

19. የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ተግባርና ኃላፊነት

**ክፍል አምስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

20. ስለ ተጠያቂነት

21. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች እና አሰራሮች

22. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

23. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**